**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

**የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና**

**የፈተናው ጊዜ፦ የ2019 ዓ.ም. የክረምት ፈተና**

**የፈተናው ቁጥር፦ 029284**

አባሪዎች፦ አባሪ ለጥያቄ 6 (ኬሪኬቸሮች)

አባሪ ለጥያቄ 7 (ኬሪኬቸር)

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የሃይማኖት ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

## በሃይማኖተኞች ት/ቤቶች ለሚማሩ

### ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች

አ. <u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. <u>የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና ሦስት ምዕራፎችን ይዟል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — | (3×13) | — 39 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — | (1×22) | — 22 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት | — | (3×13) | — 39 ነጥብ |
| በአጠቃላይ | | | — 100 ነጥብ |

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. <u>ልዩ መመሪያ</u>፦

በመልስህ ላይ ተጨባጭ <u>እውነታዎችን</u> አሳይ፥ ጠቅለል ባለ መልስ አታብቃ።

እንደ <u>ንድፍ</u> (<u>טיוטה</u>) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ የሒሳብ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) <u>በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ</u>፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ።
በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ። ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: חורף תשע"ט, 2019

**מספר השאלון: 029284**

נספחים: נספח לשאלה 6 (קריקטורות)

נספח לשאלה 7 (קריקטורה)

**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה דתי

## לעולים חדשים

## בבתי ספר דתיים

### הוראות לנבחן

א. <u>משך הבחינה</u>: שעתיים וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה שלושה פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (13×3) | — 39 נקודות |
| פרק שני | — | (22×1) | — 22 נקודות |
| פרק שלישי | — | (13×3) | — 39 נקודות |
| סה"כ | | | — 100 נקודות |

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. <u>הוראה מיוחדת</u>:

בתשובתך הבא <u>עובדות</u> ואל תסתפק בהערכות כלליות.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב <u>כטיוטה</u> (ראשי פרקים, חישובים וכדומה).

רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (39 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)።

**1.** በ18ኛው እና በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመናት በይሁዳዊያን ማኅበረሰብ ላይ የደረሱባቸው ሂደቶች ዝርዝር በፊትህ ይገኛል፦ ከአጠቃላዩ ማኅበረሰብ ጋር መዋሃድ፣ የትምህርት መስፋፋት (ማደግ)፣ የኒዮ-ኦርቶዶክስ እድገት።
ከእነዚህ ሂደቶች ውስጥ አንዱን **አቅርብ** እና ያቀረብከው ሂደት ከአዋቂነት (ኢንላይትንመንት) መለያዎች (מאפייני הנאורות) በአንዱ እንዴት ተጽዕኖ እንደተደረገበት **አብራራ**።

**2.** ከ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አሜሪካ ለብሔራዊ የሲቪል ነጻነት (ליברלית־אזרחית) ለምን እንደምሳሌነት እንደምትወሰድ **አብራራ**።
በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ የጀርመን አንድነት ለዘር-ታሪካዊ ብሔርተኝነት (אתנית־היסטורית) ለምን እንደምሳሌነት እንደተወሰደ **አብራራ**።

**3.** የፂዮን ወዳጆች ድርጅትን (אגודות חובבי ציון) ለማቋቋም ምክንያት ከሆኑት ሁለቱን **አቅርብ**።
በካቶዊስ ስብሰባ (ኮንፈረንስ) (ועידת קטוביץ) (1884) ከተሰጡት ውሳኔዎች አንዱን **አቅርብ**።

**4.** የፒል ኮሚሽን (1937) ያቀረበውን የማካፈል ሐሳብ (להצעת החלוקה) የይሁዳዊያን ሠፈራዎች የተቃወሙበትን አንድ ምክንያት **አብራራ**።
ይህ ተቃውሞ ቢኖርም እንኳን የሠፈራው መሪዎች የፒል ኮሚሽንን የማካፈል ሐሳብ ለምን እንደደገፉት **አብራራ**።

**5.** በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመሪያ (1939) ላይ በእስራኤል አገር የይሁዳዊያን ሠፈራዎች ዘንድ የብሪታኒያን ባለ ሥልጣናትን መታገሉን መቀጠል ላይ ወይም የናዚ ጠላቶችን ለማጥቃት ከእነሱ ጋር መተባበር ጉዳይ ላይ ግራ መጋባት/ማወላወል ነበር።
በእስራኤል አገር ያሉ የይሁዳዊያን ሠፈራዎች በዚህ ወቅት ያደረጓቸውን ሁለት ድርጊቶች **አቅርብ**፦ በብሪታንያ አገዛዝ ላይ ቀጣይ ትግልን የሚወክል አንድ ድርጊት እና የናዚን ጠላቶች ለመዋጋት ከብሪታንያ አገዛዝ ጋር የተደረገን ትብብር የሚወክል አንድ ድርጊት።

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## **ምዕራፍ ሁለት** (22 ነጥብ)

ከ6-7 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

### 6. አንደኛው የዓለም ጦርነት

ሀ. ለዚህ ጥያቄ በቀረበው አባሪ ሁለት ኬሪኬቸሮች አሉ። በኬሪኬቸሮቹ ላይ ለአንደኛው የዓለም ጦርነት (1914) መፈንዳት ምክንያት ለሆኑት ነገሮች ትኩረት ተሰጥቷል።
ከኬሪኬቸሮቹ አንዱን ምረጥ እና በኬሪኬቸሩ መሠረት ለጦርነቱ መንስዔ የሆነው ምን እንደሆነ **ጥቀስ**።
ይህን መንስዔ በተማርከው መሠረት **አቅርብ**።
በመረጥከው ኬሪኬቸር መሠረት የኬሪኬቸሩ ደራሲ ስለጦርነቱ መንስዔ ያለው ሃሳብ ምን እንደሆነ **አብራራ**።
(15 ነጥብ)

ለ. አንደኛው የዓለም ጦርነት ለይሁዳዊያን ወታደሮች የተለየ ችግር ፈጥሮባቸዋል።
በተማርከው መሠረት፣ ይህን ውሳኔ **አብራራ**። (7 ነጥብ)

### 7. ከግብፅ ጋር የተደረገው የሰላም ስምምነት

ሀ. ከግብፅ ጋር የሰላም ስምምነት ከተፈረመ (ማርች 26, 1979) ከሁለት ወራት በኋላ በ"ሄቤል አሚት" የ"ኔኡት ሲናይ" ሠፈራ የእርሻ ቦታ የነበረውን "קְרָהּ גן" እስራኤል አገር ለቅቃለች።
ለዚህ ጥያቄ በቀረበው አባሪ ላይ ይህን ለቅቆ መውጣት ተከትሎ በሜይ 1979 ላይ ይፋ የወጣ ሥዕላዊ መግለጫ አለ።
የ"קְרָהּ גן" መልቀቅን በተመለከተ የኬሪኬቸሩን ደራሲ ሃሳብ ከኬሪኬቸሩ በሆነ ቢያንስ አንድ ክፍል መሠረት **አብራራ**።
ከግብፅ ጋር የተደረገውን ስምምነት ለምን አብዛኛዎቹ እንደደገፉት በተማርከው መሠረት **አብራራ**።
(15 ነጥብ)

ለ. ግብፅ ከእስራኤል ጋር የሰላም ስምምነት እንድትፈራረም ያደረጓትን ሁለት ምክንያቶች **አቅርብ**።
(7 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## **ምዕራፍ ሦስት** (39 ነጥብ)

ከ8-12 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (እያንዳንዱ ጥያቄ — 13 ነጥብ)።

**8.** ናዚዎች ሥልጣን ላይ እንደወጡ (1933) ወዲያውኑ ይሁዳውያንን ከጀርመን ማኅበረሰብ ለማራቅ ከወሰዷቸው እርምጃዎች ሁለቱን **አቅርብ**።
ከኒረንበርግ ሕግ (1935) ውስጥ አንድ ዓንቀጽ **አቅርብ**።

**9.** በ"ሾአ" የ"קידוש החיים" ን ዋጋ (እሴት) **አብራራ**።
ይህን ዋጋ (እሴት) ከሚወክለው ከ"האדמו"ר מפיאסצנה" ድርጊቶች ውስጥ ሁለቱን **አቅርብ**።

**10.** በነጻነቱ ጦርነት የመጀመሪያዎቹ አራት ወራት ላይ የይሁዳዊያን የጦር ኀይሎች የወሰዷቸውን የጦርነት ዘዴዎች **አቅርብ** (እስከ ሚያዚያ/אפריל 1948)።
የ"ናህሾን" ዘመቻ (በሚያዚያ ወር 1948) በዚህ ወቅት የነበሩትን የይሁዳዊያን ሠፈራዎች የደህንነት ሁኔታ ለማሻሻል እንዴት እንደረዳ **አብራራ**።

**11.** ከተማርካቸው የእስራኤል ጦርነቶች ውስጥ፦ ከስድስቱ ቀን ጦርነት (מלחמת ששת הימים) ወይም ከአስተርዮ ጦርነት (מלחמת יום הכיפורים) አንዱን ምረጥ እና የመረጥከውን ጦርነት ስም ጥቀስ።
ለመረጥከው ጦርነት መነሳት መንስዔ ከሆኑት ሁለቱን **አቅርብ** እና በዚህ ጦርነት እስራኤልን የተዋጓትን ሀገራት ስሞች በሙሉ **ጥቀስ**።

**12.** በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻዎቹ ዐሥርታት የኢትዮጲያ ይሁዳውያን ወደ እስራኤል አገር ለመምጣት ("ዓልያ") መንስዔ ከሆኑት አንዱን **አቅርብ**።
የኢትዮጲያ ይሁዳውያን ወደ እስራኤል አገር ለመምጣት በጉዞ ላይ ሳሉ ከተገዳደሯቸው ችግሮች ውስጥ አንዱን **አቅርብ**።


**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך


# የጥያቄ 6 አባሪ — ኬሪኬቸር

## ኬሪኬቸር 'א




(**Brooklyn Eagle**, በሚባል የአሜሪካ ጋዜጣ፥ ጁል 1914 የታተመ)


## ኬሪኬቸር 'ב




<u>ትርጉም</u>፦ አፍሪካ፤ የወርቅ እርሻ (ወርቅ የሚገኝባቸው አካባቢዎች)

(http://www.boondocksnet.com)

# የጥያቄ 7 አባሪ — ኬሪኬቸር




(http://news.walla.co.il/item/3037552)